ደመመው

ቢናኙ
ቢቀኙ
ቢዘርፉ
ቢያጎርፉ
የቅኔ ነጎድጓድ
አንደበት ቢሰላ እንደቀትር እሳት
ዜማ ቢንቆረቆር
ነጋሪት ቢጎሰም
ከአጽናፍ እስከዳር
ከበሮው ቢያገሳ ጽናጽል ቢያቀጭል
ቀሳውስት ቢያረግዱ ቢሉ ዘንበል ዘንበል
ቢያዜሙ ተማህሌት
ቢያማልል ድምጻቸው ተንስኡ ያሉበት
ቅኔ ጸመድጓ እንዲሁመ አቋቋም የሚሰልሱበት
ምን ዲያቆን ቢሆኑ ቋሚ ሰሞነኛ
ከበሮ ጎሳሚ ቀዳሽ ወረበኛ
ምን ቀሲስ ቢሆኑ ቢሸከም ታቦት
ቢዘምር ዳዊትን ቢቆሙ ሳእታት
ምን ንጉስ ቢሆኑ ከቶም ስመ ጥሩ
የሚያዝ በወንበሩ
ነዋሪ ተመንበሩ
ምን ጀኔራል ቢሆን የጦርነት ቁሳር
የታክቲክ አባ ጋር
ምን ጽኃፊ ቢሆን ገዳይ በስክርቢቶ
ብእር አጣጣልን መትሮ ለክቶ
እጣውሳ ላይ ጥሎ
ወደላይ አንጋሎ
በቀይ ማገሻ
በነጭ ሰብል እርሻ
በእውቀት መዶሻ
ምን ቱጃር ቢሆኑ ሚሊዮን ቢቆጥሩ
እንቁ ቢያበድሩ
ብር ቢመነዝሩ
ወገንህ ሲደማ ቁስሉን ካላከሙ
ለፍትህ ካልቆሙ
አገርን ከጥፋት ካለተከላከሉ
የዘረኛን ተክል መንግለው ካልጣሉ
ጽናትና እምነት
ማተብ ተቀለበት
ካለተጎናጸፉ
ለእውነት ካላለፉ
ምንም መሳ የለው
እንዲያው በከንቱ ነው

ዋ ብሎ መጉረስ ነው
ትርጉም አልባ ኑሮ እርባና የሌለው
እንደሰው ተፈጥሮ
እንደ እንስሳ ኑሮ
እንደ ከብት መሞት ነው
ደመመው